ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
Re'ese Adbarat St. Mary of Debre Tsion Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, London

ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም.
13 October 2009
Ref: DTM-0215-Ext-BK-002/09

**ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት**
**አዲስ አበባ።**

**ለብፁዓን አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት (የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት)**
**በያሉበት።**

# የወቅቱን የቤተክርስቲያናችንን ችግር አስመልክቶ ከርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ለቅዱስ ሲኖዶስ የቀረበ ቤተክርስቲያንን የማዳን ጥሪ።

**"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" (ሐዋ 20፡28-30)**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በየጊዜው ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚነሱባትን አጽራረ ሃይማኖት በእግዚአብሔር ቸርነት አስታግሣ ኦርቶዶክሳዊ እምነቷንና ሐዋርያዊ ትውፊቷን ለዘመናት ጠብቃ ቆይታለች። በተለይም ለ1600 ዓመታት ያህል በእስክንድርያ ጳጳሳት ስትመራ ከቆየች በኋላ ሁሉን በጊዜው የሚያከናውን አምላክ በራሷ ቅዱስ ሲኖዶስ መመራት ከጀመረች ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ሆኗል። ቅዱስ ሲኖዶሱ ተጠሪነቱ ለመንፈስ ቅዱስ ሆኖ የቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ አስተዳደር የመጨረሻ ወሳኝ አካል እንደሆነ በቀኖና ቤተክርስቲያን በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ ተደንግጓል።

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት በፓትርያርክነት ተሰይመው ያሉት አባ ጳውሎስ ይህን ሐዋርያዊ ትውፊትና ኦርቶዶክሳዊ ቀኖና በመሻር የቅዱስ ሲኖዶስን የበላይነት ባለመቀበል ለ17 ዓመታት ቅዱስ ሲኖዶሱ በሚወስነው ውሳኔ ሳይሆን እርሳቸውና ጥቂት የጥቅም አጋሮቻቸው በሚፈልጉት መንገድ ቤተክርስቲያኗን ሲበድሏት መኖራቸውን ቀና ኅሊና ያለው ሁሉ የሚገነዘበው እውነት ነው።

ስለዚሁም ጉዳይ የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ማኅበረ ካህናትና ምእመናን በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የተለያዩ ፈተናዎች ሲቃጡ ዝም ብሎ ሁኔታዎችን በቸልተኝነት መመልከት አግባብ አለመሆኑን በመገንዘብ ከዚህ ቀደም ጥር 7 ቀን 1998 ዓ.ም. አባ ጳውሎስን "ብፁእ ወቅዱስ" ብሎ ላለመጥራትና ለፓትርያርክነታቸው እውቅና ላለመስጠት በመወሰን የአቋም መግለጫ ማውጣቷ ይታወቃል። በአቋም መግለጫውም የቤተክርስቲያኗ ራስ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ አባ ጳውሎስ በማናለብኝነት ከሚፈጽሙት በደል እንዲመልሳቸው፣ እንዲሁም በእብሪት የጣሱትን ሕገ ቤተክርስቲያን እና የገሠሡትን የራሱን የቅዱስ ሲኖዶሱን የበላይነትና መንፈሳዊ ሥልጣን እንዲያስከብር አቤቱታ ከማቅረቧም በላይ ሁኔታውን ሁሉም እንዲገነዘበውና የተቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት፣ ለጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት ለብፁአን ሊቃነ ጳጳሳት፣ እንዲሁም በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ የኢትዮጵያ

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተክርስቲያናት ቤተክርስቲያንን የማዳን ጥሪ አቅርባ ለውጡንም በትዕግሥትና በጸሎት ስትጠባበቅ ቆይታለች።

ይሁን እንጂ የተጠበቀው መልካም ለውጥ ቀርቶ **"ቤትየሰ ቤተ ጸሎት ይሰመይ፤ አንትሙሰ ረሰይክምዎ በዓተ ፈያት ወሰረቅት"** "ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል፤ እናንተ ግን የሌቦች ዋሻ፣ የቀማኞች መሸሻ አደረጋችሁት" (ማቴ፤ 21፡12) ብሎ ጌታ በወንጌል እንደተናገረው ቤተክህነቱ የዝምድና ሥራ የሚሠራበት፣ ገንዘብ ያለአግባብ የሚባክንበት፣ ከግማሽ ዕድሜያቸው በላይ የሚሆነውን ዘመን በቤተክርስቲያን ትምህርት ያሳለፉ ሊቃውንተ-ቤተክርስቲያን የሚገፉበትና የሚቸገሩበት፣ በአንጻሩ ደግሞ የአባ ጳውሎስ የሥጋ ዘመዶችና የጥቅም አጋሮች በዘረጉት የሙስና ሰንሰለት ያለልክ የሚከብሩበት ቤት ሆኗል።

ይባስ ብሎ አባ ጳውሎስና ጥቂት የጥቅም አጋሮቻቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ቤተክርስቲያንን፣ ቅዱስ ሲኖዶስንና የቤተክርስቲያን አለኝታዎች የሆኑ ብፁአን አበው ሊቃነ ጳጳሳት እንዲሁም ክቡራን ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን የሚያዋርድ ተግባር ከመፈጸም በቀር ወደ ሰላምና እርቅ የመምጣት ወይም ከጥፋት የመመለስ አዝማሚያ አላሳዩም።

በሌላ በኩል ለዘመናት ክብሯ ተጠብቆ የኖረችው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ተቆርቋሪ እንደሌላት ተቆጥሮ አጽራረ ሃይማኖት በሚያካሂዱት የፖለቲካዊነትና የጎጠኝነት ስሜት ያዘለ የጥላቻና የጥፋት ዘመቻ በጂማ፣ በኢሉባቦር፣ በአሰቦት፣ በዝቋላ፤ በደሴ፣ በጎንደር እና በሌሎችም አካባቢዎች ካህናትና ምእመናን በግፍ ሲጨፈጨፉ፣ አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ፣ ንዋየ ቅድሳት ሲዘረፉና ቅዱሳት ገዳማት በሰደድ እሳት ሲወድሙ ተገቢው መፍትሔ አለመሰጠቱ እጅግ የሚያሳዝን ነው።

ቅዱስ ዳዊት "ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር" እንዳለው ከዚህ ቀደም የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያንም ሆነ ሌሎች አድባራትና የተወሰኑ አባቶች ሲያሰሙት የነበረውን ጩኸት ብዙኀን ሊቃነ ጳጳሳት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በጥብዓት ተነስተው ስለ ሕገ ቤተ ክርስቲያን መጣስ፣ ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መፍረስ፣ ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ የበላይነት አለመከበር በአጠቃላይ አባ ጳውሎስ በቤተክርስቲያን ላይ ስለሚያደርሱት የአስተዳደር በደል፣ ስለሚያራምዱት የቤተ ዘመድ አሠራር፣ በቤተክህነቱ ስለሚፈጸመው የገንዘብ ብክነት እና ሌሎችም ችግሮች ከመናገር አልፎ የቅዱስ ሲኖዶስ የበላይነት እንዲከበር፣ የፓትርያርኩ መጠን የለሽ ሥልጣን ገደብ እንዲበጅለት፣ የሚፈጸመው ዓይን ያወጣ በደልና የሚታየው የአስተዳደር ችግር መፍትሔ እንዲያገኝ የሚያደርጉትን ጥረት እንደግፋለን።

በተለይም በአሁኑ ወቅት ቤተክርስቲያናችን የገጠማት ገደብ የሌለው ፈተና ያሳሰባቸው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ብፁአን ሊቃነ ጳጳሳት ከግንቦት 6 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ ሲካሄድ በነበረው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ወሰን የሌለው የአባ ጳውሎስ ኢ-ቀኖናዊ ፈላጭ ቆራጭ ሥልጣን ገደብ እንዲኖረው፣ የአስተዳደር በደሉ እንዲቆም፣ የቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊ ሉዓላዊነት እንዲከበር **"ሕገ እግዚአብሔር ይከበር፣ የቤተክርስቲያን ቀኖና ይጠበቅ፣ ቤቱ በሥርዓት ይመራ፤ ለ17 ዓመታት የተጣሰው ሕገ ቤተክርስቲያን ይስተካከል"** በማለት ቤተክርስቲያንን ከውርደት ለማዳን ጥረት ማድረጋቸውን በፍጹም አክብሮት እናስታውሳለን።

ይሁን እንጂ ስለቤተክርስቲያን ሰላምና አንድነት መጠበቅ ከቶውንም ቢሆን የማይጨንቃቸው ይልቁንም የቤተክርስቲያን አስተዳደር የተሻሻለ እንደሆነ ጥቅማችን ይቀራል የሚሉ አልጠግብ ባዮች ለቤተክርስቲያን አስተዳደር መቃናት ጥረት ያደረጉ ብፁአን አባቶችን መኖሪያ ቤት ለይተው በመደብደብ የፈጸሙት ውንብድና እጅግ አሳዛኝ፣ አሳፋሪም ነው። በተለይም የቤተክርስቲያናችን የአስተዳደር መቀመጫ ርዕስ በሆነው በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ግቢ በሚገኘውና ዘወትር ጥብቅ ጥበቃ የማይለየው የጳጳሳት መኖሪያ መደፈሩና የብፁዓን አባቶች መኖሪያ ቤት በር እስኪሰባበር ድረስ ሲደበድቡ፣ በማን አለብኝነት ሲዝቱና ሲሳደቡ በአባቶች ላይም ከፍተኛ የሆነ እንግልት፣ የግድያ ዛቻና ማስፈራራት ሲያደርሱ በጥበቃ ሠራተኞች ለብፁዓን

አባቶች አፋጣኝ መልስ አለመስጠቱ ለቤተክርስቲያኒቱ ከፍተኛ ጉዳትና ኃዘን እንዲሁም ከፍተኛ የታሪክ ጠባሳ ጥሎባት አልፏል።

አባቶችን በማስፈራራት፣ በአፈና፣ በዛቻ፣ በስም ማጥፋትና በአድማ የተካሄደውን የመጨረሻውን ስብሰባ በተለይም በብፁዓን አባቶች ላይ ወንጀል ተፈጽሞ፣ የቤተ ክርስቲያን ችግር ሳይፈታ በቀጠሮ ሰበብ በይደር መተላለፉን በጥልቅ ሐዘን የምናስታውሰው ሲሆን በስብሰባውም ማብቂያ በብፁዓን አባቶች እንደበት የተነገረውን እውነትና በተለያዩ የዜና አውታሮች የተላለፈውን ትክክለኛ የምስክርነት ቃላቸውን በማስተባበል በፓትርያርክ አባ ጳውሎስ የተነበበውን ማስተባበያ የተመላበት መግለጫ ፈጽመን እንቃወማለን።

**በመሆኑም የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርቲያን ካህናትና ምእመናን የሚከተለውን አቋም አውጥተናል።**

1. “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ” በማለት ሐዋርያው እንዳስተማረው ሕገ ቤተክርስቲያን እንዲከበር፣ የቅዱስ ሲኖዶስ የበላይነት እንዲረጋገጥ፣ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ድምጻችሁን በማሰማታችሁና የተቻላችሁን በማድረጋችሁ ዛቻና እንግልት ቢፈጸምባችሁም መከራውን በአኮቴት በመቀበል **“የበር መስበርና ማስፈራራት ይቅርና ለቤተ ክርስቲያን እንሞታለን፤ የቀደሙትም ሞተውላታል። አሁንም ቢሆን ወደ ኋላ አንልም”** በማለት ኃላፊነታችሁን እየተወጣችሁ ለምትገኙ አባቶቻችን ያለንን ታላቅ አክብሮት ስንገልጽ ወደፊትም ከጎናችሁ የማንለይ ልጆቻችሁ መሆናችንን ልናረጋግጥ እንወዳለን።

2. በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ግቢ የብፁአን አባቶች ማረፊያ የሆነው ቅዱስ ቦታ የወንበዴዎች ዋሻ የቀማኞች መሸሻ ከመሆን እንዲጸዳ አጥብቀን እየጠየቅን፤ በተለይም ሐምሌ 8 ቀን 2001 ዓ.ም. ምሽት ላይ የብፁዓን አባቶችን መኖሪያ በር በመደብደብና በመስበር የግድያ ዛቻ፣ ማስፈራራትና እንግልት በማድረስ የውንብድና ተግባር የፈጸሙና ያስፈጸሙ ግለሰቦችና ቡድኖች ስለፈጸሙት ወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ፤ ወደፊትም ቅዱስ ሲኖዶሱ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ መንበረ ፓትርክናውን ከወንጀለኞች እንዲያጸዳ የብፁዓን አባቶችም ህልውና በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲጠበቅ እንዲያደርግ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

3. ብዙ መልስ የሚፈልጉ የአጽራረ ሃይማኖት የክህደት ትምህርትና የቢጽ ሐሳውያን ስህተት እያለ በቤተክርስቲያን የሚታየው የአስተዳደር ብልሹነት ይወገድ በሚል ድምጻቸውን በማሰማታቸውና ጉዳዩን ለቅዱስ ሲኖዶስ ባቀረቡ አባቶች ላይ ከቤተክርስቲያን ሰዎች ሊነገር የማይገባውን ዘለፋ ያዘለ መጽሐፍ መበተን፣ ስም ማጥፋትና ሰድቦ ለሰዳቢ የሚሰጥ የአሉቧልታ ዘመቻ በጥብቅ እየተቃወምን የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ይህንን አሳፋሪ ጉዳይ መፍትሔ እንዲሰጠው በትህትና እንጠይቃለን።

4. በቤተክርስቲያን የሚታየው የአስተዳደር ብልሹነት ይወገድ በሚል ድምጻቸውን በማሰማታቸውና ጉዳዩን ለቅዱስ ሲኖዶስ በማቅረባቸው ከሥራ የታገዱ ብፁአን አባቶች ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ በጥብቅ እንጠይቃለን።

5. በአሁኑ ወቅት የሚታየውን የአስተዳደር ችግር እንዲፈታ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የተሰየመው ሰባት ብፁአን አባቶች በአባልነት የሚገኙበት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሥራውን እንዳያከናውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋሪ መንገድ የሚደረገው አፈና እንዲነሳና ሥራውን ያለምንም ተጽእኖ እንዲያከናውን እንዲደረግ እናሳስባለን።

6. ከቤተክርስቲያን ሕግ ውጪ ከየትኛውም አቅጣጫ የሚደረገውን ኢ-ፍትሐዊ የሆነ ወገናዊ ጣልቃ ገብነት እንዲቆምና ቅድስት ቤተክርስቲያንም በራሷ ሕግና ቀኖና መሠረት እንድትመራ በጥብቅ እንጠይቃለን።

7. ቅዱስ ፓትርያርክ ማለት የቅዱስ ሲኖዶስ ሰብሳቢ፣ የመላው ካህናትና ምእመናን ተቀዳሚ አባት፣ የቅድስት ቤተክርስቲያን ጠባቂ፣ ከሥጋዊና ዓለማዊ አስተሳሰብ ርቆ ስለቤተክርስቲያን አንድነት መጠበቅ፣ ስለምእመናን ደኅንነት በጾም በጸሎት ተግቶ የሚሠራ እንጂ ከታላላቁ እስከ ጥቃቅኑ ሥራ ድረስ በሁሉ ያለ አግባብ ጣልቃ የሚገባ ማለት አይደለም። ለዚህ ሁሉ ችግር ምክንያቱ ቅዱስ ሲኖዶስ በ1991 ዓ.ም. ባወጣው ሕገ ቤተክርስቲያን አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 15 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ፣ ማዕከላዊነትን ባለማክበር የቅዱስ ሲኖዶስን ውሳኔ በመጣስ አባ ጳውሎስ በማንአለብኝነት የሚፈጽሙት ተግባር ነው። ይኸው ከሕገ ቤተክርስቲያን ውጪ የሆነው የአባ ጳውሎስ ኢ-ቀኖናዊ ፈላጭ ቆራጭ ሥልጣን ገደብ እንዲደረግለትና ሕግ ተላልፈው የሚፈጽሙት ተግባር እንዲቆም አጥብቀን እንጠይቃለን።

8. መላው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ብፁአን አባቶች ከአባ ጳውሎስ የከፋፍለህ ግዛው ሴራ ተጠብቃችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ደሙ በመሠረታት ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ለተፈጠረው ችግር ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት የቀድሞ ብፁአን አባቶችን አሠረ ፍኖት በመከተል በፆም በጸሎት፣ ሌት ተቀን ደከመን ሰለቸን ሳትሉ አንድ ሆናችሁ ቤተክርስቲያንን ከችግር በመታደግ አባታዊና ታሪካዊ ግዴታችሁን እንድትወጡ በታላቅ ትሕትና እንጠይቃለን።

9. መላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካህናትና ምዕመናን በተከሰተው ኢ-ክርስቲያናዊና ሕገ ወጥ ነገር ተስፋ ባለመቁረጥ እንደዚሁም ደግሞ የቤተክርስቲያናችንን አንድነትና ሰላም ለማይሹ አጽራረ ሃይማኖት ቦታ ባለመስጠት ከምንም በላይ ለቅድስት ቤተክርስቲያን አንድነትና ሰላም መጠበቅ፣ ለቅዱስ ሲኖዶስ የበላይነት መረጋገጥ፣ ለሕገ ቤተክርስቲያን መከበር በጥብዓት ከተነሱ ብፁዓን አባቶቻችን ጎን በመቆምና አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ በማድረግ የበኩላችንን አስተዋጽኦ እንድናደርግ ሃይማኖታዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

የሰላም አምላክ ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያናችን ሰላምን ይስጥልን።
የእምነ ጽዮን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን።
አሜን።

ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

ጥቅምት 3 ቀን 2002 ዓ.ም፣
ለንደን፤ ብሪታንያ።

<u>ግልባጭ፦</u>

- ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ።

- ለመላው የኢ/ኦ/ተ/ቤ አህጉረ ስብከት ጽ/ቤት
  በያሉበት።